# አገር እንዴት ሰነበተች?

## ከአዲስ አበባ  በታሪኩ አወቀ ተጽፎ የተላከ የምስክርነት ደብዳቤ

ሰላም ለማከብርህ ጓዴ ከሰማኸኝ በላይ፣ከነቤተሰብህ እንደምን አለህ?እኔ ደህና ነኝ ።ምንም እንኳን እንደምታውቀው ለእናቴ ቀብር አዲስ አበባ ስሄድ ብትሸኘኝም አሁን ግን ከዚያ የበለጠ ሃዘን ውስጥ ነኝ። የእናቴን ሃዘን ሳልወጣው ትልቅ ሃዘን ደርሶብኛል።ይህ ሃዘን ግን የእኔ ብቻ ሳይሆን የሁሉም ኢትዮጵያዊ፣ የአንተም ጭምር ከባድ ሃዘን ነው።

ብዙ ጊዜ እያነሳን የምንወያይበት፣የሚያስጨንቀንና የሚያሳስበን ያገራችን ሁኔታ ከሚጠበቀው በላይ ሆኖ አገኘቸዋለሁ።የድህነቱ ፣የኑሮ ውድነቱ፣የሰላም ማጣቱና የስጋቱ ደረጃ መለኪያ አላገኘለትም።እራስ ወዳድነቱም የዚያኑ ያህል ነው።ምን መአት እንደ ወረደ አይታወቅም። በሰፈረተኛው፣በጎረቤት ቀርቶ በቤተሰብ መካከል ያለው ግንኙነት ከመሻከሩም በላይ እንደ ደበኛ ይተያያል፤አይተማመንም። አንዱ ሌላውን ለማጥቃት ቀን ቆርጦ የተቀመጠ ይመስላል።ብቻ ምን አለፋህ አድፍጦ ዋሻው ውስጥ የተኛ አውሬ ወይም ጅብ ሆኗል ብልህ ማጋነን አይደለም።የግል ጥቅም ሁሉንም ቀፍድዶ ይዞታል፤ከራሱ በላይ ለሌላው አያስብም፤ለዛሬው እንጂ ለነገው ኑሮው አይጨነቅም።ስለ አገርማ ማሰብ ጅልና ኋላ ቀር ተደርጎ ይታያል።ምን አለፋህ በሰው ጭንቅላት ውስጥ የትልቋ አገር  ፍቅር ሳይሆን የድንጋይ ክምር የምኞት ሕንጻ ተገንብቶበታል።ሁሉም ጨዋታ የሚያጠነጥነው በሕንጻና በቪላ ቤት  ዙሪያ ሆኗል።በውጭ አገር ለአስር ዓመት ከኖርክ የአንድ ትልቅ ሕንጻ ባለቤት መሆን ይጠበቅብሃል።ያ ከሌለህ እንዳለህ አትቆጠርም።በውጭ አገር መኖር ወርቅ ሲያፍሱ መኖር እንደሆነ የሚቆጥሩ መኖራቸው ላያስገርም ይችላል፤ምክንያቱም በውጭ አገር የሚኖረው አገር ውስጥ ገብቶ የሚያደርገው ቅብጠትና መዝናናት እውነተኛ ኑሮውን ሸፍኖታል።አብዛኛው ወጣት ይህንን ሲያይ እኔም ከአገር ወጥቼ ይለፍልኝ በማለት ድንበር ጥሶ፣ባሕር አቋርጦ ለመውጣት የሚያስበው በጣም ብዙ ነው።በጉዞም ላይ ሕይወቱን ያጣው ቀላል ቁጥር አይደለም።በዬአገሩ እስርቤትማ የሚማቅቀውን ቤቱ ይቁጠረው።በዬሰፈሩ ድንኳን ተጥሎ መንገድ ላይ ሞተ የሚለው መርዶ የተለመደ ሆኗል።ሌላው ይህንን መርዶ እንደቀላል ይቆጥረዋል።አሥሮቹ ሞቱ ሲባል መቶዎቹ መንገድ ይገባሉ።

በወጣቱ በኩል የሚታዬው በአገሩ  ተስፋ መቁረጥና ግዴለሽነት የነገዋ ኢትዮጵያ ምን ልትመስል እንደምትችል አመላካች ነው።ደንታቢስና ምግባረቢስ ሆኗል።ምን ይፈረድበታል! ስርዓቱ በኮተኮተው ማህበረሰብ የሚወለድ ልጅ ምን አይቶ ይደግ ትላለህ?ትውልድ እኮ የሚቀረጸው በሰፈነው ስርዓትና በከባቢው ነው።ስርዓቱ ጨካኝ፣ ዘራፊና ጎሰኛ ከሆነም ያንኑ ይዞ ያድጋል፤የሆነውም ያው ነው።አሁን ሰው የሚታዬው በሰውነቱ ሳይሆን በጎሳ ማንነቱ ነው።በጎሳ ማንነቱ ይጠቀማል ወይም ይጎዳል፤ያገኛል ወይም ያጣል፤ይሸለማል ወይም ይቀማል፤ ይሾማል ወይም ይሻራል፤ይታሰራል ወይም ይፈታል።ምን አለፋህ እጣፈንታህ የሚወሰነው በጎሳህ ወርድና ቁመት ነው።ቤቱ፣ሥራው፣ሁሉም አስፈላጊ ነገር በጎሳህ ማንነት ታገኛለህ፤ወይም ታጠዋለህ።  ጊዜ ካነሳው ጉልበተኛ ጎሳ ከሆንክ የማይከፈትልህ በር የለም።አርጋጅ አስረጋጅህ ብዙ ነው።ታዲያ ምንም የኑሮ ውድነቱ ቢከብድ በጎሳ መንኮራኩር የምትወጣበት ዘዴና ጉልበቱን አታጣም፤ ዕድሜ ለጎሳዬ ብለህ የምትኖርበት ወይም ጎሳህን የምትረግምበት ወቅት ላይ መሆናችንን ካዬሁት በመነሳት ስገልጽልህ ስሜትህን ለመጉዳትና ተስፋ ለማስቆረጥ  ሳይሆን መፍትሔ ለመፈለግ የችግሩን ጥልቀት እንድታዬው በማሰብ ነው።ስሜትህን ጎድቸው ከሆነም ይቅርታ አድርግልኝ።እኔም ያደረብኝ ስሜት ስለሆነ ለብቻህ አይደለህም፤አብረን ነን፣አብረንም መፍትሔ ለመፈለግ እንድንነሳ ያደርገናል እንጂ በፍርሃት አደንዝዞ አይለያዬንም፤ለያይቶም አያጠፉንም።ሰው በመከራ ጊዜ ይፈተናል ይባላልና ይህንን ፈተና ሰው ሆነን እንደምናልፈው ጥርጣሬ የለኝም።

ይልቅስ በሰሞኑ ያዬሁትንና የታዘብኩትን ላጫውትህ፤-አንዳንድ የማውቃቸው ሰዎች ለእናቴ ሞት የመጣሁ መሆኔን ሳያውቁ ለዲያስፖራው ክተት ጥሪ የመጣሁ እዬመሰላቸው የጎሪጥ ያዩኛል።ቀረብ ብዬ ሳናግራቸውና የመጣሁበትን ምክንያት ሳስረዳቸው ግን ያ በጥርጣሬና በንቀት ብሎም በጥላቻ የተሸፈነ ፊታቸው ወደ

መልካምና ሃዘኔታ ገጽ ሲለወጥ ለማዬት ችያለሁ።እግዚአብሔር ያጥናህ!!በማለትም  ለአመጣጤና ለሃዘኔ እውቅና ይሰጡታል።እውነት ነው ዲያስፖራ በተባለው ስብስብ ላይ ሕዝቡ ያለው አስተያዬት ከስርዓቱ ነጥሎ የሚያዬው አልሆነም።ሁሉም ስራዓቱን በሚያይበት ዐይኑ ያዬዋል።የስርዓቱ ደጋፊ  ያሞግሰዋል፣ተቃዋሚ ደግሞ ዓይንህን ላፈር ይለዋል።

እኛ በውጭ የምንኖረው ሰዎች ደግሞ የዲያስፖራ ስብስቡ እነማንን እንዳካተተ በደንብ እናውቀዋለን፣ለምሳሌ እኔና አንተ ተሳቢ የምንለው ተሰማ ወልዴ፣ ያ የግንቦት ሰባቱ የለንደኑ ግብረሃይል ጥሩምባ ነፊ  በብዙዎቹ ተሴ ጥሩምባው በመባል የሚታወቀው አሁን በሰሞንኛው የቤተመንግሥት እራት ግብዣ ላይ ከተኮለኮሉት መሃል ተቀምጦ ሳዬው ስለሱ አፈርኩለት።ያፈርኩለት ለምን እዛ ቦታ የመዋል ክብር አገኘ(ክብር ከተባለ)ብዬ ሳይሆን ምን አይነት ሥራ እዬሠራ ፣ምን አይነት ኑሮ እንደሚኖር እያወኩት አሁን አገር ቤት ውስጥ ገብቶ በፈረንጅ አገር ያውም በእንግሊዝ አገር ኑሮ  የደላው ሰው መስሎ ፣ለእራት ግብዣው የሚከፈለውን ብዙ ዶላር ቢያንስ 500 ፓውንድ ለመክፈል መቻሉ ስላስገረመኝ ነው።በመንግሥት ድጎማ ቤት ኪራይ ውስጥ እዬኖረ፣ በሳምንት ለምግብ 50 ፓውንድ እያገኘ፣ በፓኪስታኖች ሱቅ ውስጥ ዕቃ በመደርደርና በጽዳትሥራ በሰዓት ከሶስት ፓውንድ በማይበልጥ  ጥቁር ክፍያ፣ምሳና እራቱን ከፓኪስታኖቹ ጋር ቻፓቲና ሩዝ እዬበላ የሚተዳደር መሆኑን የምናውቀው  ነው።እሱ ብቻም አይደለም  በተቀመጠበት ጠረጴዛ ላይ የተኮለኮሉት  የምናውቃቸው የሱው ቢጤ የግንቦት ሰባት መንጋዎች ናቸው። ሌሎችም በተለያዩ አገሮች በተመሳሳይ ኑሮ የሚኖሩ መሆናቸውን የሚኖሩበት አገር ኑዋሪ የሚመሰክረው ብቻ ሳይሆን  ስታያቸው የተመቻቼ ኑሮ እንደማይኖሩ ታውቃለህ።

በዚህ ግርግር የቦታና የቤት ስጦታ እናገኛለን ብለው የገቡ ጥቂቶች አይደሉም።በንግድ ሥራ ላይ ያውም በሸቀጣ ሸቀጥ፣ካገርቤት በርበሬና እንጀራ ሳይቀር የሚቸረችሩ የሱቅ ባለቤቶችና ሠራተኞች ፣በታክሲ ሾፌርነት፣ በድርጅት ዘበኝነት፣በግለሰብ ቤትና በሆቴሎች የጽዳት ሥራ ላይ የተሰማራው የቤተመንግሥቱ  እራት በሌ ብዙ ነው። ዘርዘር አድርገን ካዬነው የሚከተለውን ይመስላል።

ሀ/ በፈረንጅ አገር ለብዙ ዓመት የኖረ፤ዕድሜው የገፋ፣ ከመሸ አገሬ ገብቼ ቁራሽ መሬት ወይም ኮንደሚኔም አገኝቼ በማገኛት የጡረታ ገቢ ኑሬ ልሙት ብሎ የሚመኝ፣የውጭ አገር ኑሮ የሰለቸው፣

ለ/ከማንኛውም ስርዓት ጋር በጥቅም የሚተሳሰርና የተሳሰረ፣በንግድ ዘርፉ ተሰማርቶ ገንዘብ መሰብሰብ ዓላማው የሆነ፣አገሩንም ሽጦ ቢሆን ገንዘብ ካገኘ ቅር የማይለውና የማያቅማማ፣ገንዘብ አምላኩ

ሐ/በጎሳ ቅርጫት ውስጥ ተጠቅጥቆ የድርጅትና የግለሰቦች በተለይም የኦነግና የግንቦት ሰባት ደጋፊና  ተከታይ የሆነ ንቃተ አልባ ባተሌ፣

መ/በፕሮቴስታንት እምነት ተጠምቆ የሥርዓቱን መሪዎች ጣኦት አድርጎ የተቀበለና በሌሎቹ ሃይማኖቶች በተለይም በኦርቶዶክስና በሙስሊም ላይ  ጥላቻ ያለው ጭፍን

ሠ/በጣም ጥቂቱ አገሩንና ወገኑን የረዳ መስሎት ከአገር አጥፊው የጎሳ ስብስብ ከሆነ መንግሥት ጋር ተጣብቆ ሃብታም ለመሆን እምነት ያደረበት የተምታታበት ጅል አይሉት መርህ አልባ ፣እያዬና እዬሰማ የማይገባው በድን

እንግዲህ ዲያስፖራ ማለት በእኔ እይታ ከላይ በተዘረዘሩት ሰልፎች ውስጥ የተሰገሰገ ቡድን ነው።ኢትዮጵያዊው አገር ወዳዱማ በማንነቱ፣በኢትዮጵያዊነቱ አይደራደርም፤ኢትዮጵያዊ እንጂ ዲያስፖራ ነኝ ብሎ አይመጻደቅም። የኔና ያንተም ፣የሌሎቹም አቋም ይኸው ነው።

አሁን ላይማ ሲውል ሲያድር መስገብገቡን አይቶ ሕዝቡ ዲያስፖራ የሚለውን ስያሜ ትቶ ጆቢራ እያለው መጥራት ጀምሯል።እውነትም ጆቢራ! ይሉኝታ የሌለው ሁሉን ልብላ፣ላግኝ፣ልያዝ የሚል ግልገል አንሳ!

የክፍለ ከተማዎችንና የአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤትን የመሬት ስሪት ቢሮ፣የቤት ግንባታ ድርጅቶችን(ሪያል ስቴትን) ጽ/ቤቶች ያጨናነቀው ይኸው ዲያስፖራ ተብዬው መሬት አዳኝ ስብስብ ነው። እንደው ለወሬው እንጂ ብዙሃኑ ከፍሎ ለመግዛት እንደማይችል ልቦናው ያውቀዋል።ከመንግሥት በኩል መሬት ቢሰጠውም ሊሰራበት ሳይሆን ሸጦ ገንዘቡን ለመብላት ነው።ታዲያ በዚህ ከንቱ ስብስብ የተነሳ ሁሉም በውጭ አገር የሚኖረው ኢትዮጵያዊ የተጠላ ሆኗል።እኔም አንተም የዚያ ሰለባዎች ሆነናል።

በዚህ ስብስብ ላይ ማዕቀብ ሊጣልበት ይገባል፤ አድርባይ ተብሎ ከማህበረሰቡ ሊነጠልና ሊገለል ይገባል። በነጋዴውም ላይ እንዲሁ ያለመግዛት አድማ መምታት ምናልባት ሊታረም የሚችልበት ዘዴ ይሆናል።በደቡብ አፍሪካ ከዘረኞች መንግሥት ጋር ተባባሪ በነበሩት የንግድ ተቋማት ላይ የተወሰደው ቦይኮት የማድረግ እርምጃ ውጤታማ እንደሆነው ሁሉ በእኛም አገር ለጎሰኛ ስርዓት ተባባሪና አቀባባይ በሆኑት ላይ የገቢ ምንጫቸውን በማድረቅ፣ካዝናቸውን በማራቆትና  በማመንመን ተመሳሳይ እርምጃ ቢወሰድ ውጤታማ ይሆናል ብዬ አስባለሁ።

በጣም የሚገርመው ነገር ዲያስፖራው በቤተመንግሥቱ ለእራት ከፍሎ በተሰበሰበበት ቦታ ላይ አብይ አህመድ ያደረገው ንግግር ነው። ወዶ የገባን አህያ አሳምረህ ጫነው እንዲሉ! ምንም እንኳን ከአንድ ሚሊዮን በላይ የተጠበቀበት የከተት ጥሪ ባይሳካም ጥቂት ሰዎች የተካፈሉበት የእራት ግብዣው ገቢ ሚሊዮን ባይሞላና፣ ወጭውን ባይሸፍንም 800 ሽህ ዶላር እንዳስገባ ይፋ ሆኗል።ዲያስፖራው ለመንግሥት ገንዘብ ሲያስገባ አብይ አህመድ ደግሞ በምላሹ አስገብቶለታል።

በዛ እራት ላይ ለተካፈሉት አሸርጋጆች የተላለፈው መልእክት ግን ጆሮ ይዞ እንደመስደብ ይቆጠራል።

በተችዎች በኩል ውሻን ባጥንቱ ዲያስፖራን በፍትፍቱ እዬተባለ በተሰየመው በዚህ የእራት ግብዣ ላይ አብይ አህመድ ከተናገራቸው ውስጥ ሲጨመቁ የሚከተሉት መልእክቶች(ስድቦች ወይም ወቀሳዎች) ይገኙበታል ።

1/ ህሊና ቢሶች ናችሁ፤ነገራትን አታስተውሉም፣ስለዚህ ለማስተዋልና ለማስታወስ ሞክሩ፣

2/አዲስ አበባ (ፊንፊኔ)ውስጥ መሬት እናገኛለን ብላችሁ አታስቡ፤ ስትፈልጉ ያለማ ባዶ ቦታ ጎርጎራ ስላለላችሁ እዛ ሂዱ፣ቦታው ለሁሉም የተመቼ ነው፣ውሃ፣ጫካ፣ሜዳ፣ተራራ አለው።አንድ ሚሊዮን ዶላር ካላችሁ እኛ በምናወጣው እቅድና ፕላን የሚሠራ ቪላ ቤት ባለቤት ትሆናላችሁ።ያም ብቻ አይደለም ለገንዘብ ያላቸውን ስስ ብልት ሲነካ ቤቱን በዓመት ለአስራ አንድ ወር አከራይታችሁ ገንዘብ ታገኛላችሁ፤አንድ ወሩን ትዝናኑበታላችሁ ሲል የሕልም እንጀራ አጉርሷቸዋል።ከሚሊዮን ዶላር በታች ያላችሁ ሰዎች ግን አታስቡት ሲል እቅጩን ነግሯቸዋል፤ይህ ለተሴ ጡሩምባውና ለመሰሎቹ ትልቅ መርዶ ነው።

3/እዚህ ካላችሁት ውስጥ 90% እዚህ በመገኘታችሁ(በመብላት በመጠጣታችሁ)ደስተኞች ናችሁ ብዬ አምናለሁ፣ለወደፊቱም በተመሳሳይ መንገድ እንደምትካፈሉ ተስፋ አደርጋለሁ። ሌላም ሌላም ነገር

4/ ከእስር ስለፈታቸው የሕወሃት ወንጀለኞች የተምታታና እርስ በራሱ የሚጋጭ ማብራሪያም ሰጥቷቸዋል። ከወራት በፊት በጦርነቱ ውስጥ እያለን የተወሰነ ነው፣ከጦርነቱ በኋላ በመንግሥት ደረጃ አባይ ግድብ ዳርቻ ተቀምጠን  በካቢኔ አባላት የተወሰነ ነው፣ይልና ቀጠል አድርጎም በፍትሕ ሚኒስትሩ በኩል ተወስኖ ዝርዝሩን ስናዬው ደንግጠናል ይላል።ዝርዝሩን አይቶ አይሆንም ለማለት ግን አለመድፈሩ የራሱም ውሳኔ መሆኑን እዛው በዛው ያረጋግጣል።አላፊነቱንም ለፍትህ ሚኒስትሩ ለጢሞቲዎስ አሸክሞታል።በዚህም አላበቃም  በማንም የውጭ አገር መንግሥትም ሆነ ሃይል ትዕዛዝና ጥያቄ የተወሰነ ሳይሆን በእግዚአብሔር ትዕዛዝ እኔ የወሰንኩት ውሳኔ ነው፣እግዚአብሔር ፍታቸው አለኝ ፈታኋቸው---ወዘተ በማለት ከተጠያቂነት ለማምለጥ አንድ ጊዜ በካቢኔ አባላቱ ፣ሌላጊዜ ደግሞ  በፈጣሪ ላይ ደፍድፎታል።በተለመደው መንገድ የማይያዝ የማይጨበጥ ማምታታት የተሞላበት ማብራሪያ ነው።ይበልጥ ላብራራ ባለቁጥር ይበልጥ ከቅጥፈት አዘቅት ውስጥ ይነከራል። እንደዚህ በደቂቃዎች ውስጥ የተናገረውን የሚዘነጋው አብይ አህመድ ሌላውን ወገን የማስታወስ ችግር ያለበት እያለ ይሰድባል፣ያዋርዳል።

5/ስለወታደራዊ ሹመት አሰጣጡም እንዲሁ በጎሳ ተዋረድ ለባለተረኛው የኦሕዴድ ኦነግ አባላት የተሰጠ ላለመሆኑ የሄደበት መንገድ ሁሉ ዓይናችሁን ጨፍኑ ላሙኛችሁ ከሚል ብልጣ ብልጥነት ተለይቶ አይታይም። በጣም የሚያናድደው ደግሞ አገር በታታኝ የሆነ ሕገመንግሥትና የክልል አወቃቀር ተሸክሞ ኢትዮጵያ አትበታተንም፣ልዑላዊነቷን አሳልፈን አንሰጥም እያለ መቀደዱ ነው። ይህንን ደረቅ ውሸት እዬሰማ ከማጨብጨብ ባለፈ ደፍሮ የጠዬቀ ግብር በሌ ዲያስፖራ የለም።

6/እጅግ በጣም የሚያበሳጨው ደግሞ ኢትዮጵያ ጠላት የላትም የሚለው አነጋገሩ ነው።ዲያስፖራው ሳይቀር ኖ ሞር እያለ በውጭ አገር ከተሞች ተሰልፎ ያወገዘውን የውጭና የውስጥ ጠላቶች ደባ፣ብዙ አገር ወዳድ የተሰዋበትን የጠላቶች ጥምር ጥቃት ፣ወረራና አገር የማፍረስ ዘመቻ የጠላቶች ሴራ አይደለም ሲል የሞቱትን አገር ወዳዶች ብቻ ሳይሆን ለአገር ልዑላዊነትና ዳር ድንበር፣ለአገር ህልውና በጦር አባላቱ በኩል የተከፈለውን የሕይወት ዋጋ ማጣጣል ብቻ ሳይሆን ንቀትና ድፍረት ነው።ለዳግመኛም ወረራ ጠላት የለብህምና ዝም ብለህ ተቀመጥ ብሎ የማዘናጋት መልእክት ያስተላለፈበት ነው። አሁን ኖ ሞርም ማለት አይገባም፣ኢትዮጵያም ጠላት የላትም ሲል የታሪካዊ ጠላት የሆነችውን ግብጽን፣ከዓመት በላይ የኢትዮጵያን ድንበር ጥሳ መሬት የያዘችውን ሱዳንን፣በተደጋጋሚ ከውጭ ጠላቶች ጋር ተሰልፋ ያጠቃችንንና ያስጠቃችንን፣ አሁንም በብዙ ጫናዎች ለማምበርከክ የምትዝትብንን አሜሪካንንና አጫፋሪ የአውሮፓ መንግሥታትን ጠላቶች አይደሉም ብሎ በማቅረቡ ከክህደት በላይ ክህደት ፈጽሟል። ለምን ጥቅም እንደሆነ ግን ግልጽ ነው፤ ያም ለተወነጀለበት ክስ ማምለጫና ለሥልጣኑ መደላደል ይረዳኛል ከሚል ግላዊ ፍላጎት የተነሳ መሆኑን ሕዝቡ አውቆታል። ፤ ያልተረዳውና ያልጠዬቀው በጥቅም አገኛለሁ ጉጉት ጀሮና ልቦናው የተደፈነው ዲያስፖራ ብሎ የሚጠራውና በሆዱ የገዛው ስብስብ ብቻ ነው።

ጉደኛው ግብር በሌው ዲያስፖራ ግን በተቃርኖዎች በተሞላው መግለጫ መካከል ጭብጨባውን አቅልጦታል።ሳይገባው የቀረ ደናቁርት ቢሆን እንጂ የገባው ቢሆን ኖሮ፣ለእውነትና ለአገሩ ክብር የቆመ ቢሆን ኖሮ አዳራሹን ጥሎ ለመውጣት በተግደረደረ ነበር፤ ወይም ደፋር አገር ወዳድ ቢሆን ኖሮ እዛው ላይ በጥያቄ ባፋጠጠው ነበር።ግን ከዚህ ስብስብ የሚጠበቅና ስብእናውም የሚፈቅድለት አይደለም።አስተባባሪ ነን የሚሉትም ሰዎች ያደረጉት ፍሬ ከርስኪ ንግግር የዚያ አመላካች ነው። አብይ አህመድ በተነፈሰ ቁጥር ጭብጨባው ይቀልጣል፤ ሲስቅባቸው ጭብጨባ፣ሲሳደብ ጭብጨባ፣ሲዋሽ ጭብጨባ! ሲዝት ጭብጨባ፣ምን አለፋህ! በአዳራሹ ውስጥ በተሰበሰበው መካከል ፣በጭብጨባ ማን ያሸንፍ ከሚል ውድድር ውስጥ የተገባ ይመስላል።ተቀምጦም ቆሞም ጭብጨባ ነው።ማጨብጨብ የፍርሃትና የክህደት፣የእበላ ባይነት መግለጫና ማወደሻ ሆኗል ብልህ እንዳትታዘበኝ።በመሬት ላይ ያለው ጥሬ ሃቅ ያው ነው።ቸብ፣ ቸብ፣ቸብ፣ ቸብ--ቿ ቿ ቿ ቿ ቿ--

እነዚህን በረከተ መርገሞች እንደ ውዳሴ ተቀብሎ የእጁ መዳፍ እስኪላጥ ድረስ ያጨበጨበው ዲያስፖራ ተብዬው ሆዳም ስብስብ ስለአገሩ አንድነትና ክብር፣ስለሕዝቡ መከራና ብስቁልና፣ የወደፊት አደጋ፣ ምንም ጥያቄ ሳያነሳ በማሞገስና በማወደስ ብቻ አብይ አህመድ ለዘላለም ይኑር እያለ! ከቤተመንግሥቱ የምግብ አዳራሽ ወጥቶ ሄዷል።ክፉ ሆድ ይቀደድ!

ይህንን ጉድ የታዘበው ሕዝቡም ግራ ከመጋባቱም በላይ በዲያስፖራው ላይ ንቀቱንና ብስጭቱን ከመግለጽ አልተቆጠበም።እዬገለጸም ነው።

ወዳጄ ሰማኸኝ ከዚያማ በኋላ ምን ልበልህ በውጭ አገር በመኖሬና በአንድ ሙቀጫ ዲያስፖራ ተብሎ መወቀጡ ሲሰማኝ አፈርኩ።ያለን አማራጭ ዲያስፖራ አለመሆናችንን፣በኢትዮጵያዊነት መንፈስ ተነስተን ለኢትዮጵያና ለሕዝቡ በሚጠቅመውና በሚያስከብረው ተግባር ላይ መዋል ነው።ቤትና ንብረት እኮ የሚታሰበው አገር ሲኖር ነው። ከቻልኩኝ በቅርቡ ካሉት የፋኖ ጦር ተወካዮች ጋር ለመገናኘት እሞክራለሁ። ለማገናኘትም ሰው ቃል ገብቶልኛል።ሕዝቡ ተስፋ ያደረገው እነሱን ነው።መንግሥት ግን በፍርሃት ሊያጠፋቸው ብዙ እዬጣረ ነው። የኦነግ ጦር እንዳሻው ሕዝብ ሲያርድ፣ሲያፈናቅል፣ከተማ ውስጥ ሲሰበሰብ፣ በመንግሥት መኪና ሲንሸራሸር፣በመከላከያው የጦር መሳሪያና ሜካናይዝድ ትጥቅ አገር ሲያሸብር እንዳላዬ

የሚያልፈው የኦሕዴድ መራሹ መንግሥት ተብዬው ከማን ጎን እንደቆመ በግልጽ አሳይቷል።የአማራው መኖሪያ መሬቱ በትግሬ ወራሪ ሃይል ተይዞ፣አሁንም የአፋሩ መኖሪያ በከባድ መሣሪያ እዬተደበደበና ሕዝቡ እዬሞተና እዬተፈናቀለ የጦርነቱ ተጠናቀቀ ወሬ ለምን ዓላማ መናፈስ እንደተፈለገ የሚያሳዩ ብዙ ሃቆች አሉ።ፋኖ ደግሞ ምህዳሩን እያሰፋ በመምጣት ላይ ነው።በአማራው ክልል በተባለው ብቻ የተወሰነ ሳይሆን የኢትዮጵያን ቅርጽ በያዘ መልኩ ከየአቅጣጫው ያገሪቱ ክፍሎች እኔም ፋኖ ነኝ በሚል መርሆ አማራ ያልሆነው ጭምር ባለበት ቦታ ድምጹን እያሰማና ትግሉን እዬተቀላቀለው መምጣቱን ከታማኝ ምንጮች በኩል ሰምቻለሁ።ይህ ስሜት ካደገና ከተጠናከረ የአገራችን ትንሳኤ እውን ይሆናል፤እንዲሆንም መርዳትና ማጠናከር ይጠበቅብናል።ወያኔ አሁንም የአማራውንና የአፋሩን መኖሪያ በወረራ እንደያዘና ለዳግመኛም ሰፊ ወረራ ሃይሉን እያሰባሰበ ይገኛል። ከተባባሪው ኦነግ አሸባሪ ቡድን ጋር አገር እያመሰ ነው።አብይ አህመድና የሚመራው መንግሥትም ይህንን ሁሉ ሽንፈት ከዶ ኢትዮጵያ አሸንፋለች እያለ ይቀደዳል።ከወያኔም ጋር ለመወያዬት ሽርጉድ እያለ ነው።ለሱ የትግራይ፣የወሎና የአፋር ሕዝብ እንደ ኢትዮጵያ ሕዝብ የሚቆጠሩ አይመስለኝም፤ለሱ ኢትዮጵያ ማለት የሥልጣን ወንበሩ ብቻ ናት።

የሕዝቡ አሰላለፍና በተለይም የአማራው መነሳሳት ያስደነበራቸው የኦነግ ቤተሰቦች ከያሉበት ተጠራርተው በመምከር ላይ ናቸው።ከእስርቤት የተፈቱት እነጁዋር ሙሃመድና የድርጅታቸው የኦፌኮ አባላት ሌሎቹም ከየሚኖሩበት አገር ከአሜሪካና አውሮፓ እንደጅብ ተጠራርተው ወደ አገር ገብተዋል።መረራ ጉዲና፣ለማ መገርሳ፣ከነዚሁ ውስጥ ናቸው።ለሰላማዊ ድርድር ሳይሆን በመካከላቸው ያለውን ልዩነት አሶግደው የሚመኙትንና የቆሙለትን ኢትዮጵያን የመቆጣጠር አለያም አፍርሶ ኦሮሚያ የሚባል አገር የመፍጠሩን ዓላማቸውን ለማሳካት ነው።ይህን ለማሳካት ደግሞ አማራውንና ሌላውን አገር ወዳድ ማጥፋት ቀዳሚ ግባቸው ነው።ለዚያም ከውጭም ከውስጥም ካለው አጥፊ ሃይል ጋር ከመተባበር ወደኋላ አይሉም። ስለሆነም አገር ወዳዱ ሊመጣ የሚችለውን አደጋ ተገንዝቦ እራሱንም አገሩንም ለማዳን ይበልጥ መደራጀት አለበት፣ የጀመረውን ሕዝባዊ ጦር፣ሃይል ማጠናከር ይገባዋል።መዘናጋቱ ከጥፋት አያድነውም። በሸለብታ ውስጥ የሚገኘው የአዲስ አበባ ሕዝብ ከእንቅልፉ መንቃት አለበት።የጭዳው ግንባር ቀደም እሱ መሆኑን መረዳት ይገባዋል።

የጥምቀቱ በዓል አከባበር ሌላው የሕዝብ ትግል የታዬበት መድረክ ነው።በኢትዮጵያዊነቱ የሚያምነው ሕዝብ የጥምቀቱን በዓል ሽፋንና ምክንያት በማድረግ ለሰንደቅ ዓላማው ያለውን ክብርና ፍቅር የገለጸበት አጋጣሚ ነበር።በመንግሥት ትዕዛዝ በተሰማሩ የፖሊስ አባላት የሰንደቅ ዓላማ አረንጓዴ ቢጫና ቀይ ቀለም ያለውን ማንኛውንም አልባሳት ከሰው ትከሻና ከአልባሳት መደብር እዬቀማ ቢወስድም፣ለባሹንና ሻጩንም ቢያንገላታም እምቢ ባይነቱ የበለጠ እየተጠናከረ ሄደ እንጂ ሊቀንሰው አልቻለም።ሕዝብ ከቆረጠና በአቋሙ ከጸና ማሸነፉ የማይቀር መሆኑ በጥምቀቱ በዓል የተገኘው ድል ማረጋገጫ ነው።የጥምቀት በዓሉ ኦነግና ኦህዴድ በሚቆጣጠሩት ጥቂት ቦታ ካልሆነ በስተቀር ከዳር እስከዳር ከሁሉዬውም በበለጠ መልክ በኢትዮጵያ ሰንደቅ አላማ አጊጦና አሸብርቆ፣ደምቆ ተከብሯል።ለበዓሉድምቀትና ሰላም የሙስሊም እምነት ተከታዮችም ትልቅ አስተዋጽኦ አድርገዋል።የፍቅርና የአንድነቱን ታሪክና ባሕል በተግባር አሳይተዋል። ለታቦቱና ለምእመናኑ ባሳዩት ክብርና የማስተናገድ ተሳትፎ የጠላቶችን የከፋፍለህ ግዛ መመሪያ አሽቀንጥረው ጥለውታል።ይህ አንድነት ጸንቶ እንዲቆይ ከክርስትና እምነት ተከታዮችም በኩል እስከሁለዬውም ለሙስሊሙ የሚያደርገውን ወገንተኝነት ሊቀጥልበትና ሊንከባከበው ይገባዋል። አክራሪዎችን ሙስሊሙም ክርስቲያኑም ሊዋጉት ይገባቸዋል።አገር ከሃይማኖትና ከጎሳ በላይ ናት! ለእምነት ተቋማት መኖር አገር መኖር አለባት፤ለአገር አንድነትና ነጻነት ሁሉም ዘብ መቆም ይኖርበታል።

በከተራውና በጥምቀተ-ባሕሩ እለት ሙሉ በሙሉ በሚል ደረጃ በሰላም ተከብሮ መዋሉን በንዴትና በቅናት ያዩት ኦነጋውያን በቀጣዩ የቃናዘገሊላ ክብረበዓል እንዳይደገም ለማድረግ የኦሮሙማው የጥፋት ሃይሎች በመንግሥት ተብዬው ወታደሮችና ፖሊሶች ታጅበው የሚካኤልና የማርያም ታቦቶች ወደ ቤተመቅደሳቸው እንዳይገቡ በፈጠሩት የጥቃት እርምጃ ከምእመናኑ በኩል የሦስት ንጹሃን ሕይወት ያለፈ ሲሆን ብዙዎችም ቆስለዋል፤ቁጥራቸው የማይታወቅም በዬእስር ቤቱ ታጉረዋል።ሙታኑን ለመቅበርም ቤተሰብ አስከሬን ተነፍጎት ማስፈራሪያ ሳይቀር ደርሶታል።ይህንን ወንጀል ያስፈጸመው በአብይ አህመድ የሚመራው የኦሮሙማው

የብልጽግና መንግሥት አመራሮችና ተጠራርተው የተሰባሰቡት የአነግ ቤተሰቦች መሆናቸውን ብዙዎች በማስረጃ እያጋለጡት ይገኛሉ። እነጃዋር ሙሃመድ የሚነዱት ቄሮ የተባለ የደንቆሮዎች ስብስብ እስከዛሬ ድረስ ድምጹን አጥፍቶ አሁን ላይ መነሳቱ ከመሪዎቹ መፈታትና ትዕዛዝ ጋር የተቆራኘ ለመሆኑ አጠያያቂ አይደለም።

ኦህዴድ መራሹ መንግሥት በተለያዩ ጊዜያቶች የሕዝቡን ትኩረትና ተቃውሞ ለማዘናጋት የተለያዩ ችግሮችን መፈልፈሉን የምናውቀው ነው።ከጥምቀቱ በዓል ቀደም ብሎ በመስቀል አደባባይ ምክንያት የተነሳው ውዝግብ አንዱ ሲሆን በሕዝቡ ተቃውሞ ጋብ ያለ ቢመስልም የመጨረሻ መፍትሔ አግኝቷል ማለት አይደለም። የተንጠለጠለ የቀውስ ቋጠሮ ፣ወይም የታመቀ ቦምብ ነው።ብዙ ሌሎች የቀውስ ምክንያቶች እንደሚከሰቱ ካለፉት ተደጋጋሚ ድርጊቶች ተምረን ልንዘጋጅ ይገባል። በተቃዋሚ ስም የተኮለኮሉት የፖለቲካ ድርጅት ነን ባዮች በተለይም የሥልጣን ቁራሽ ያገኙት ማንን እያገለገሉ መሆናቸውን ቆም ብለው ሊያስቡት ይገባል። ማንነታቸው የሚታወቀው ከአሁን በኋላ በሚወስዱት አቋማቸው ይሆናል። ያላቸው ምርጫ ካለው ጎሰኛ ስርዓት ጋር ተጣብቆ መቀጠል አለያም ከሕዝቡ ጋር ተሰልፎ ትግሉን መምራት።ትግል ሲባልም ለጥገና ለውጥ ወይም ለተመሳሳይ ባርነት የሚዳርግ የግለሰቦችና የድርጅቶች ለውጥ ሳይሆን የቀውሶች ፈጣሪ የሆነውን፣በጎሳ ህሳቤ የተመሰረተ ስርዓት ለአንዴና ለሁሌው ለማሶገድ የሚችል፣ለባዕዳን መሳሪያ ያልሆነ የአገርን ዳር ድንበር የሚያስከብር አገር ወዳድ መንግሥትና ስርዓት ለማስፈን የሚያበቃ፣ መሆን ይኖርበታል። ያ ካልሆነ ግን ከአጋም የተጠጋ ቁልቋል ሆኖ ሲያለቅሱ መኖር ነው። ሊታረምና ሊሻሻል የማይችል የአገር ነቀርሳ የሆነውን የጎሳ ስርዓት ካላሶገዱት በቀር ሰላም፣አንድነትና እድገት አይኖርም።ከኢትዮጵያ አልፎ ለሌላው የአፍሪካ አገር የሚተርፍ አገር አጥፊ ልክፍት ነው፤ለዳግመኛ የቅኝ አገዛዝ በር ይከፍታል።የጎሳ ፖለቲካ የሰብአዊ መብት ማስከበሪያ የዴሞክራሲ ጽንሰሃሳብ ሳይሆን የሰብአዊ መብት ጸር፣የዴሞክራሲ ጠላት፣ የድንቁርና መግለጫ ፣ የአውሬነት መፈልፈያ ቀፎ ነው።ባርነትን ፈቅዶ ለመቀበል የሚሰለፉበት አሳፋሪ ጎራ ነው።

ለጊዜው ላካፍልህ የመረጥኩት ይህንን ይመስላል።አንተም በበኩልህ ይህንን ለምታውቃቸው ሁሉ አጋራቸው፣ እውጭ ላለው ኢትዮጵያዊ በሚደርሰው መንገድ ለማሰራጨት ሞክር። አንተም ሆንክ ሌላው በሌሎቹ የዜና ምንጮች እንደምትከታተሉ ባውቅም በእኔ በኩል በገሃድ የታዘብኩትን ስልክልህ ለሰማኸው ማረጋገጫ ይሆናል ብዬ አምናለሁ።

የእናቴን አርባ ቀን አውጥቼ ከሶስት ሳምንት በኋላ አመለሳለሁ፤ቀሪውን በዝርዝር ስንገናኝ አጫውትሃለሁ። እስከዚያ ድረስ ግን ማወቅ ያለብህ ጉዳዮች ካሉ አሳውቅሃለሁ።

እስከምንገመናኝ ደህና ሁንልኝ፤ለቤተሰብህ ሰላምታ አቅርብልኝ።

ያንተው ታሪኩ አወቀ

ተጻፈ ጥር 14 ቀን 2014 ዓም፣አዲስ አበባ